# የተከራዮች መብቶች

# በኮቪድ-19 (COVID-19) በሽታ ወቅት

## (ሰኔ 15 ቀን 2020 የተሻሻለ)

<u>የኪራይ ክፍያና ከቤት የመባረር ሁኔታ</u>

በኮቪድ-19 (Covid-19) ምክንያት ስራዬን አጣሁ ወይም አገኝ ከነበረው ገቢ በአሁኑ ወቅት ገቢዬ ዝቅ ብሏል። የቤት ኪራይ የግድ መክፈል አለብኝን?

ግን በኪራይ መክፈል ላይ የኪራይ መርጋት እንዳለ ሰምቼ ነበር። ታድያ ይሄ ምን ማለት ነው?

ኪራይ መክፈል ካልቻልኩ አከራዬን ክራይ መክፈል አልችልም ብዬ መንገር አለብኝን?

የቤት ኪራዬን መክፈሌን ማስተካከል የምችል አይመስለኝም። መውጣት ነው ያለብኝ ግን ውሌን ላፈርስ እችላለሁን

የቤት ኪራይ አልከፈልክም ብሎ አከራዬ ቢከሰኝስ ምን ይሆናል?

አከራዬ ከቤት እንድወጣ ሊከሰኝ ስንት ጊዜ ይፈጃል።

ከኮቪድ -19 (Covid-19) በፊት አከራዬ ከሶኛል፤ ጉዳዬ አሁን ምን ይሆናል?

በጉዳዬ ላይ ውሳኔ ተወስዷል፤ የምወጣበትም ቀን ተመድቦልኝ ነበር።  አሁን ምንድነው ነው የሚሆነው ?

የቤት ኪራዬን ወደ ፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት( Court Registry) እንዳዴም “ የመጠበቅያ ትእዛዝ” በመባል ወደሚታወቀው እንድከፍል ታዝዤ ነበር። አሁን ፍርድ ቤቱ ዝግ ነው። ፍርድ ቤቱ በተዘጋበት ወቅት የቤት ኪራይ ክፍያዎቼን ምን ላርጋቸው ?

<u>የቤት ሁኔታ ጉዳይ</u>

የቤቴ አከራይ፤ ቤቴ ውስጥ ግብቶ የቤቱን ሁኔታ ማየት አለብኝ እያለ እያስቸገረኝ ነው። ቤቴ ውስጥ ማስገባት ግዴታ ነውን?

አስቸኳይ የሆነ ጥገና የሚያስፈልገው ነገር በቤቴ ውስጥ አለ። አከራዩ እስኪያሰራው ድርስ መጠበቅ አልችልም፤ አከራዩ ማበጀት አለበትን ?

ከኮቪድ በፊት በቤቴ ውስጥ ጥገና የሚያስፈልጋቸው ነገሮች ነበሩ፤ አሁን ግን የቤቴ አከራይ አሻፈረኝ በማለት ነው።ጥገናውን የግድ አከራዩ ማድረግ አለበት ማለት ነውን?

<u>ዋጋቸው ዝቅ እንዲል የተደረጉ ቤቶች ጉዳይ</u>

ገቢዬ ጎድሏል። ምን ላድርግ?

**እንደገና የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኘሁበት ዕለት ዓመት በዚህ ኮቪድ ባለበት ወቅት ነው። ታድያ ይህንን ዓመታዊ የማረጋገጫ ጉዳይ እንደገና በዚህ ዓመትም ማድረግ ይጠበቅብኛልን?**

**በዚህ በኮቪድ የወረርሽኝ በሽታ ወቅት፤ የዲሲ የቤቶች ባለስልጣን የምከፍለውን የቤት ኪራይ ሊጨምርብኝ ይችላልን?**

**በዚህ በኮቪድ የወረርሽኝ በሽታ ወቅት፤ የዲሲ የቤቶች ባለስልጣን የምከፍለውን የቤት ኪራይ ሊጨምርብኝ ይችላልን?**

**በመንግስት ቤት ውስጥ ነው የምኖረው። የዲሲ የቤቶች ባለስልጣን ( DCHA) ኪራይ መክፈል ቢያቅተኝ ከቤቴ ሊያባረኝ ይችላልን ?**

**ከኮቪድ በፊት፡ በኩፖኑ ፕሮግራም፤ ከቤት መውጣት አለባቸው የሚል ሃሳብ ያለበት ወረቀት አግኝቼ ነበር። እኔም ጉዳዩ እንዲሰማ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ነበረኝ፡ አሁን የሚሆነው ምንድነው?**

**ከኮቪድ-19 (Covid-19 በፊት፤ መልሼ እከፍላለሁ የሚል ስምምነት ከዲሲ የቤቶች ባለስልጣን (DCHA) ጋር ፈርሜአለሁ። አሁን ግን ስራዬን ስላጣሁ መክፈል አልቻልም። ምን ላድርግ?**

## የኪራይ ክፍያና ከቤት የመባረር ሁኔታ (Rental Payments and Eviction Cases)

### በኮቪድ-19 (Covid-19) ምክንያት ስራዬን አጣሁ ወይም አገኝ ከነበረው ገቢ በአሁኑ ወቀት ገቢዬ ዝቅ ብሏል። የቤት ኪራይ የግድ መክፈል አለብኝን?

**አዎን።** ተከራዮች የሚከፍሉት ባይኖራቸውም የቤት ኪራይ የግዴታ መክፈል አለባቸው። የገንዘብ እርዳታ ሊያገኙ የሚችሉባቸው ምንጮች አሉ። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎን በኦንላይን resource guide ይመልከቱ። በኮቪድ-19 (Covid-19) ምክንያት፤ የቤት ኪራይ መክፈል እንደማይችሉ አከራዮ እንዲያውቀው መንገር ጥሩ ነው።

**ግን በኪራይ መክፈል ላይ የኪራይ መርጋት እንዳለ ሰምቼ ነበር። ታድያ ይሄ ምን ማለት ነው?**

ይህ ማለት በግለሰቦች ቤቶች ወይም ቅናሽ ባልተደረገባቸው ቤቶች ወስጥ የሚኖሩ ከሆነ፤ አከራዮ፤ በዚህ በኮቪድ ግዜ የኪራይ ዋጋ ሊጨምር አይችልም ማለት ነው።ግን የኪራይ ገንዘባቸውን በነበረበት ዋጋ፤ የግድ መሰብሰብ አለባቸው።

**ኪራይ መክፈል ካልቻልኩ አከራዬን ክራይ መክፈል አልችልም ብዬ መንገር አለብኝን?**

በአጠቃላይ አነጋገር፤ በዚህ በኮቪድ (Covid-19) ምክንያት ኪራይ መክፈል አልችልም ብሎ ለአከራይ መንገር ጉዳት የለበትም። በወጡት አዲስ ህጎች አንዳንድ ጠቀሜታዎችን ለማግኘትም፤ አስቀደመው ለአከራይ መንገር አለ።

በኮቪድ (Covid-19) ምክንያት ገንዘባዊ ችግር ካጋጠሞት፤ አከራዮ፤ ኪራዮን ለመክፈል የተጨማሪ ቀናት የሚሰጦት መሆኑን በማመልከት የክፍያ ስምምነት የሚል ጽሁፍ መፈረም አለበት። ብዙ ግዜ ግን የሆነ ዓይነት ስምምነት ከመፈረሞ በፊት፤ ጠበቃን ማናገር ይጠቅማል። ምክር ለማግኘትና ጉዳዮን በተመለከተ እገዛ እንዲደርግሎት ለማመልከት፤ወደ ተከራዮች አስቸኳይ መስመር (Tenant Hotline) በስልክ ቁጥር 202-851-3388 ይደውሉ።

ከአከራዮ ጋር ከተነጋገሩ፡ያንን ስምምነት ለመፈረም ገና ዝግጁ አይደለሁም፤ ተጨማሪ ግዜ ያስፈልገኛል ማለት ምንም አይደለም። የገንዘብ እርዳታ ለማግኘትም በመሞከር ላይ መሆንዎን ወይም የሚያውቁት ከሆነ፤ ገቢ ማግኘት መቼ እንደሚጀምሩ ለአከራዮ ሊያሳውቁ ይችላሉ። እንደገና የቤት ኪራዮን ለመክፈል ዝግጁ ካልሆኑ በስተቀረ ስምምነቱን መፈረም የለቦትም።

**የቤት ኪራዬን መክፈሌን ማስተካከል የምችል አይመስለኝም። መውጣት ነው ያለብኝ ግን ውሌን ላፈርስ እችላለሁን**

በአጠቃላይ፤ ከግዜው በፊት ውሉን ለማፍረስ የአከራዮ ፈቃድ ያስፈልጎታል። አብዛኛውን ግዜ፤ አከራይ ሌላ የሚከራይ ሰው ካላገኘ በስተቀረ፤ ለተቀሩት ወራት ክፍሉ ማለት ይችላል። ወር ወር ለመክፈል የተስማሙ ተከራዮች ግን የ 30-ቀን ማስታወቅያ ከሰጡ መልቀቅ ይችላሉ። ከወር እስከ ወር የሚከፈል ዓይነት ኪራይ እንዳሎት በሚመለከት ጥያቄ ቢኖሮት ለማወቅ ወደተከራዮች አስቸኳይ መስመር በስልክ ቁጥር 202-851-3388 ለምክርና ጉዳዮን በተመለከተ እርዳታ ለማግኘት ይደውሉ።

### የቤት ኪራይ አልከፈልክም ብሎ አከራዬ ቢከሰኝስ ምን ይሆናል?

ቤቱን መልቅቅ አለቦ የሚል ማስታወሻ ከአከራዮ ሲያገኙ ወይም አከራዮ ፍርድ ቤት ቢከሶ፤ <u>ያኔውኑ አይደለም</u> ከቤት መውጣት ያለቦት። አማራጮች አሎት። በዲሲ ህግ መሰረት፤ቤት ኪራይ ባለመክፈል ቢከሰሱ ፤ ከቤት ከመባረሮ በፊት ዕዳዎን በመክፈል እንደገና የተከራይ መብቶን ለማደስ መብት አሎት። መከራከርያ ነጥቦችም ሊኖሮ ይገባል። ጉዳዮን በሚመለከት እርዳታና ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ወደ ተከራዮች መስመር  በስልክ ቁጥር 202-851-3388 ደውሉ።

### አከራዬ ከቤት እንድወጣ ሊከሰኝ ስንት ጋዜ ይፈጃል።

አዲስ የዲሲ ህግ፡ አዲስ ከቤት ማስወጣት ጉዳዮች በሙሉ እንዲቆሙ አዟል። A new D.C. law stops all new eviction case filings. ይህ ግዜያዊ ህግ ነው። የሚሰራውም ይህ ህግ የሚሰራው ኮቪድ እስካለበትና ከዛም በኋላ ላሉት 60 ቀናት ብቻ ነው። ለአሁኑ፤ እስከ መስከረም 22 ቀን 2020 አዲስ ጉዳዮች ቆመዋል። ይህ ህግም፤ የዲስትሪክቱ ከንቲባ የኮቪድን አስቸኳይ ግዜ ሁኔታ እንዲራዘም ካላደርገ/ገች ነው።

በተጨማሪም፤ የሚኖሩበት ቤት በማእከላዊው መንግስት ቅናሽ የተደረገባቸው ህንጻዎች ውስጥ ከሆነ ወይም አከራዮ፤ ቤቶቹን የገዛው በመንግስት በሚደገፉ አበዳሪዎች ከሆነ፡ አዲስ የመንግስት ህግ፤ እስከ ነሓሴ 24 ቀን 2020 ፤ ኪራይ አልከፈሉም ብሎ ሊከሶትና ከቤት ሊያስወጣዎት አይችልም።ለዚህም አስቀድሞ የ 30 ቀናት ማስጠንቀቅያ መስጠት አለበት።

የአከራይና የተከራይ ፍርድ ቤት( Landlord Tenant Court )፤ በአሁኑ ግዜ እስከ ሰኔ 19 ቀን 2020 ድረስ ዝግ ነው። ይህም ማለት አከራዮ ይውጡልኝ ብሎ እንኳን ቢከሶ፤ እስከ ሰኔ ወር መጨረሻ ወይ እስከ ሃምሌ ወር መጀመርያ ፍርድ ቤት አይቀርቡም። አከራዩ ከከሰሶት፡ ፍርድ ቤቱ የሚቀቡበትን ቀን በጽሁፍ የይገልጽሎታል። አከራዩም የፍርድ ቤት ጥሪ ወረቀቱንም ለእርሶ መስጠት አለበት።

ጥያቄ ቢኖሮት ወይም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፤የተከራይ አስቸኳይ መስመር ወደ (Tenant Hotline) በስልክ ቁጥር 202-851-3388 በመደውል ለእርዳታ አመልክቱ

### ከኮቪድ -19 (Covid-19) በፊት አከራዬ ከሶኛል፤ ጉዳዬ አሁን ምን ይሆናል?

ከዚህ ከወረርሽኝ በሽታ በፊት ቀነ ቀጠሮ ተይዞላቸው የነበሩ ጉዳዮች ሁሉ ቢያንስ እስከ ሰኔ 19, 2020 ተላልፈዋል። በአንድ ወቅት፤ ጉዳዮ ተሰርዟል ወይም ተላልፏል የሚል ጽሁፍ ከፍርድ ቤት ያገኛሉ። አዲስ ቀን ሲመደብ፡ ይህ ቀን ያለበት ማስታወሻ ያገኛሉ። ጉዳዮን በተመለከተ ኦንላይን online ገብተው ማየት ይችላሉ። ጉዳዮን በተመለከተም በኦንላይ ሊፈልጉት ይችላሉ ወይም ወደ ተከራይ አስቸኳይ መስመር (Tenant Hotline) በስልክ ቁጥር 202-851-3388 በመደወልም እኛ አዲሱ የፍርድ ቤት ቀጠሮዎ መቾ እንደሆነ ልንይሎት እንችላለን።

### በጉዳዬ ላይ ውሳኔ ተወስኗል፤ የምወጣበትም ቀን ተድቦልኝ ነበር።  አሁን ምንድነው ነው የሚሆነው ?

ከቤት የመባረር ጉዳዮች በኮቪድ ምክንያት ቢያንስ እስከ ሃምሌ 24 ቀን 2020። የቤት የማስወጣት ስራ ሲጀመር፡ አዲስ የ21 ቀናት ማስጠንቀቅያ ይላክሎታል።

**የቤት ኪራዬን ወደ ፍርድ ቤቱ መዝገብ ቤት( Court Registry) እንዳዴም “ የመጠበቅያ ትእዛዝ” በመባል ወደሚታወቀው እንድከፍል ታዝዤ ነበር። አሁን ፍርድ ቤቱ ዝግ ነው። ፍርድ ቤቱ በተዘጋበት ወቅት የቤት ኪራይ ክፍያዎቼን ምን ላርጋቸው ?**

የቤት ኪራዮን በሁለት ዓይነት መንገዶች መክፈል ይችላሉ። ከቻሉ ከእነዚህ ሁለት አንዱን ተጠቅመው ኪራዮን ይክፈሉ። ስለዚሁ ጉዳይ ከጠበቃ ጋር ሊነጋገሩ ከፈለጉ የአከራይ አስቸኳይ መስመር (Tenant Hotline) ን በስልክ ቁጥር 202-851-3388 ይደውሉ።

መጀመርያ በኦንላይን መክፈል ይችላሉ። ወደ LTPayPort@dcsc.gov ኢሜል ከላኩ ወይም በስልክ ቁጥር 202-879-4879 ከደውሉ በኦንላይን እንዴት እንደሚከፍሉ መመርያዎችን ሊያገኙ ይችላሉ። የባንክ አካውንት ካሎ፤ የአካውንት መረጃዎን በመስጠት $1 ይከፍላሉ።በክሬዲት ካርድ ወይም በዴቢት ካርድ መክፈል ከፈለጉ የ If you pay የ2.5% ክፍያ አለ። ይህ ማለት ደግሞ ለምሳሌ የሚከፈል $1,000 በተጨማሪ $25 ይከፍላሉ ማለት ነው። <u>ይህ ከፍተኛ ዋጋ ነው ስለዚህ ከዚህ ዓይነት አከፋፈል ይቆጠቡ።</u>

ሁለተኛ፤ ፍርድ ቤቱ እስኪከፈት ድረስ በቀጥታ ለአከራዩ ሊከፍሉ ይችላሉ ። ባንክ አካውንት ከሌሎት የበለጠው አማራጭ ይህ ነው። ይህም፤ ያንን ከላይ የሚከፈለውን ገንዘብ ያስወግድሎታል። በቀጥታ ለአከርዮ ከከፈሉ ማረጋገጫ ወረቀት መያዝ አለቦት። ይህንን ላላማድረግ ግን ምክንያት ካሎት፤ ለምሳሌ የገንዝብ ትእዛዝ (ማኒ ኦርደር)ለማሰራት ወይም ወደ ቤት አከራይ ጽህፈት ለመሄድ፤ ከቤት መውጣት የማይችሉ ከሆነ፤ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝዙን እንዲቀይር መጠየቅ ይችላሉ።

## <u>የቤት ሁኔታ ጉዳይ Housing Conditions Issues</u>

**የቤቴ አከራይ፤ ቤቴ ውስጥ ግብቶ የቤቱን ሁኔታ ማየት አለብኝ እያለ እያስቸገረኝ ነው። ቤቴ ውስጥ ማስገባት ግዴታ ነውን?**

“ምክንያታዊ በሆነ ጉዳይ” አመቺ በሆነ ሰዓት፤ የቤትዎ አከራይ ቤትዎ ውስጥ መግባት ይችላል።ይህንንም ሲያደርግ የ48 ሰዓታት ማስጠንቀቅያ ሊሰጥ ይገባል። በዚህ ባለንበት የኮቪድ ግዜ የአከራዮ ቤትዎ ውስጥ መግባት “ ምክንያታዊ” ሊሆን አይችልም ብለው መከራከር ይችላሉ በተለይ እርሶ በዕድሜ የገፉ ከሆኑና አደገኛ የጤና ችግር ካላቦትና አስቸኳይ መሰራት ያለበት ነገር ከሌለ፤ ፍጹም ቤትዎ ውስጥ ሊግባ አይችልም።

በመሆኑም ለአከራዮ በጽሁፍ ምክንያቶችዎን በመግለጽና በሌላ አመቺ ግዜ ሊደረግ እንደሚችል በማስረዳት ጉብኝቱ ምክንያታዊ አይደለም በማለት ሊቃወሙ ይችላሉ። እንዳው በደፈናው ካለምክንያት አከራዮ ቤትዎ ውስጥ እንዳይገባ ከከለከሉ፤ ውሉን አፍርሰዋል በማለት ሊከሶትን የ30ቀናት ማስጠንቀቃ ሰጥቶ ከቤት ሊያባርሮት ይችላል። ይህ ከሆነ ወደ ተከራይ አስቸኳይ መስመር በስልክ ቁጥር 202-851-3388 ደውለው ምክር ሊጠይቁና ለተጨማሪ እርዳታ መመዝገብ ይችላሉ።

**አስችኳይ የሆነ ጥገና የሚያስፈልገው ነገር በቤቴ ውስጥ አለ። አከራዩ እስኪያሰራው ድርስ መጥበቅ አልችልም፤ አከራዩ ማበጀት አለበትን ?**

አዎን። አስቸኳይ ጥገናዎች በአከራዩ ነው መደረግ ያለባቸው።ይህ የዲሲ የቤቶች ባለስልጣንንም( D.C. Housing Authority (DCHA) ሆነ ሌሎች የግል አከራዮችን ይመለከታል።አስቸኳይ ጥገናዎች ሲባል የእሳት አደጋ ሊያስከትል የሚችል፤ የመጸዳጃ ክፍል ብልሽት፤ የሰገራ ቱቦዎች ብልሽት፤ የተሰበሩ መስርያዎች፤የውሃ ቱቦዎች መቀደድ፤ጎርፍ፤ በአከራዩ የተደረጉ የኤሌክትሪክ፤የውሃ፤ የጋዝ መጥፋት የመሳሰሉ ይገኙበታል ግን ሌሎች ኢያሌ ነገሮችንም ያጠቃልላል።
**አስተውሉ፤ በዚህ ባለንበት የኮቪድ አደጋ፡ ማናቸውም የኤሌክትሪክ፤ የውሃ፤ የጋዝ ድርጅቶች፤ የኢንተኔት አቀባዮችም ጭምር አገልግሎታቸውን መስጠት ሊያቋርጡ አይችሉም።**

አስቸኳይ ጥገና የሚያስፈልገው ነገር ሲያጋጥም፤ አከራዮን ወድያውኑ ማሳወቅ አለቦት። ou should notify your landlord immediately of any emergency repair needs. የቤቶ አከራይም ሆነ ሌሎች የሚጠግኑ ሰዎች፤ ቤትዎ ውስጥ መግባት ቢኖርባቸው፤ በተቻለ መጠን ይህንን ተረድተው፤ በኮቪድ ምክንያት ከሰው ጋር የመገናኘት ችግር ወይም በዕድሜ የገፋ ሰው በቤትዎ ውስጥ ካለ አንድ ዓይነት የማግለያ ዝግጅት ማደረግ አለቦት። አከራዮ የትገናውን ስራ ማከናወን አለበት። ጥገና የማያደርግ ከሆነ፤ የገበያተኛና የቁጥጥር ጉዳይ ክፍል (Department of Consumer and Regulatory Affairs (DCRA) መጥተው ሁኔታውን እንዲመረምሩ መጋበዝ ይችላሉ። ተከራዮች በስልክ ቁጥር 202-442-9557በመደወል ወይ online በመግባት መጥተው የሚያዩበትን የቀጠሮ ቀን ማመቻቸት ይችላሉ። አብዛኛዎቹ የአስቸኳይ ጥገና ጉዳዮች በአካል ተመጥቶ ነው የሚታየው። ሁሉም የሚመጡት ኢንስፔክተሮችም አስፈላጊውን የጤና ጥበቃ ሽፋኖችን ያደርጋሉ።

የቤት አከራዮ፤ እነኚህን ጥገናዎች ካላደረገ፤ የአስቸኳይ ሁኔታ ክስ ፍርድ ቤት ሊያቀርቡ ይችላሉ። ፍርድ ቤቱ አሁንም የአስቸኳይ ሁኔታዎችን ጉዳዮች ይቀበላል።በዚህ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ መረጃ ወይም እርዳታ ማግኘት ካስፈለጎ ፤ ወደ አከራይ አስቸኳይ መስመር (Tenant Hotline) በስልክ ቁጥር 202-851-3388 ይደውሉ።

**ከኮቪድ በፊት በቤቴ ውስጥ ጥገና የሚያስፈልጋቸው ነገሮች ነበሩ፤ አሁን ግን የቤቴ አከራይ አሻፈረኝ በማለት ነው። ጥገናውን የግድ አከራዩ ማድረግ አለበት ማለት ነውን?**

የቤት አከራዮ ሁልቀን የቤቶች ህጎች ከሚሉት ወይም ከሚጠይቁት ጋር መጓዝ አለበት። Your landlord is always required to maintain your home in compliance with housing regulations. ጥገና ያስፈልገዋል ተብሎ አንዴ ከተነገረ፤ በተወሰነ ግዜ ውስጥ ጥገናውን ማከናወን አለበት። በአሁኑ ወቅት ያከውን የወረረሽኝ በሽታን ግምት ውስጥ በማስገባት፤ አከራዮ አንዳንድ ትንናሽ ጥገናዎችን በማድረግ በኩል የመዘግየት ሁኔታ ሊያጋጥም እንደሚችል ሊከራከር ይችላል። እርሶም ደህንነትንና የአኗኗር ሁኔታን የሚነኩ ጥገናዎች፤ ኮቪድ እስኪያልቅ ድረስ መጠበቅ አይችሉም ብለው መመለስ ይችላሉ።

አከራዮ እነኚህን ጥገናዎች የማያደርግ ከሆነ፤ የገበያተኛና የቁጥጥር ጉዳይ ክፍል (DCRA) መጥተው እንዲመለከቱ ጋብዙ። አስቸኳይ ላልሆኑ ነገሮች፤ በኦንላይን online ገብተው ወይም በስልክ ቁጥር 202-442-4400 ደውለው ቀጠሮ መውሰድ ይችላሉ። አስቸኳይ ያልሆኑ ጉዳዮች ቨርቹዋሊ( virtually) ወይም በስልክ ወይም በኮምፑተር በሚደረግ መተያየት ይደረጋሉ። በዚህም ዲሲ-አር-ኤ (DCRA) ተከራዮች የእጅ ስልካቸውን በመጠቀም ይህ እንዴት እንደሚካሄድ ያሳያል። ይሁንና፤ አስቸኳይ ላልሆኑ ጉዳዮች፤ አከራይና ተከራይ የተመደበው ግዜ ካልተመቸ፤ ለሌላ ግዜ ለማስተላለፍ ከፈለጉ ዕድል ይሰጣል

የተከራይ አስቸኳይ መስመርን (Tenant Hotline) በስልክ ቁጥር 202-851-3388 በመደወል፤ ይህንን አስቸኳይ ያልሆን ጥገናን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ን ምክር ከተፈልገ ከእኛ ጋር ተገናኙ።

## <u>**ዋጋቸው ዝቅ እንዲል የተደረጉ ቤቶች ጉዳይ**</u> (Subsidized Housing Issues)

### ገቢዬ ጎድሏል። ምን ላድርግ?

በገቢዎ ላይ አንድ ለውጥ ሲኖር **ወድያውኑ** ወደ ዲሲ የቤቶች ባለስልጣን( DCHA) ያስታውቁ።

- <u>የቤት ምርጫ ኩፖን ፕሮግራም (Housing Choice Voucher Program)</u>፤ ኢሜል ካሎት፤ ይህንን መረጃ ለዲሲ የቤቶች ባለስልጣን (DCHA) በ ሚከተለው አድራሻ hcvpcovid19interim@dchousing.org ኢሜል አድረጉ። ወደ ዲሲ የቤቶች ባለስልጣንም በስልክ ቁጥር 202-535-1000 በቀጥታ በመደወል ገቢዎን እንዳጡ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።

- <u>የህዝብ (የመንግስት) ቤቶች (Public Housing)፤</u> ኢሜል ካሎት፤ይህንን መረጃ ወደ ዲሲ የቤቶች ባለስልጣን (DCHA) በሚከተለው አድራሻ phcovid19interim@dchousing.org ኢሜል ያድርጉ። የርሶን የቤቶች አስተዳደር ጽህፈት ቤትንም በማግኘት፤ እንደገና የመቆየት ጉዳይን በሚመለከት ምን መንገድ እንደሚከተሉ ጠይቋቸው።

ስለዚሁ ጉዳይ ጥያቄ ካሎት ወይም ኢሜል የሌሎት ከሆነ ወደ ተከራይ አስቸኳይ መስመር(Tenant Hotline) በስልክ ቁጥር 202-851-3388 ይደውሉ።

**እንደገና የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኘሁበት ዕለት በዚህ ኮቪድ ባለበት ወቅት ነው። ታድያ ይህንን ዓመታዊ የማረጋገጫ ጉዳይ እንደገና በዚህ ዓመትም ማድረግ ይጠበቅብኛልን?**

የዲሲ የቤቶች ባለስልጣን (DCHA) አሁንም ገና የእንደገና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶችን እየመረመረ ነው። በመሆኑም የሚያስፈልጉ ዶኩመንቶች ካሉበተቻለ መጠን ለማስገባት ሞክሩ። መልሱ በፕሮግራሙ ላይ ካለው ትንሽ ይለያያል፤

- የቤት ምርጫ የኩፖን ፕሮግራ (Housing Choice Voucher Program) ውስጥ የሚሳተፉ ከሆነ፤ ዶኩመንቶችዎ ሁሉ፤ ለ ዲሲ ቤቶች ባለስልጣን ( DCHA)፤ በፖስታ ወይም በሚከተለው አድራሻ 1133 North Capitol Street NE. በሚገኝ ሳጥን ውስጥ በማስቀመጥ፤ መሰጠት አለበት። ዶኩመንቶቹን ለማስገባት የሚቻሎትን ሁሉ አድርጉ። ግን ባለስልጣኑ፤ ተካፋዮች፤ እንደገና የማረጋገጫምስክር ወረቀት ካላገኙ፤ በዝህ በኮቪድ ምክንያት ቢያንስ እስከ ሚያዝያ 24 ቀን 2020 ይባረሩ የሚል አስተያየት አደግፍም።

- የህዝብ(የመንግስት) ቤቶች (Public Housing) ተቀማጭ ከሆኑ፤ የቤቶች አስተዳድር ጽህፈት ቤትዎ ጋ ተገናኝተው አስፈላጊ ዶኩመንቶችን በሚመለከት ምን መመርያዎች መከተል እንዳለቦት ይጠይቁ።

**በዚህ በኮቪድ የወረርሽኝ በሽታ ወቅት፤ የዲሲ የቤቶች ባለስልጣን የምከፍለውን የቤት ኪራይ ሊጨምርብኝ ይችላልን?**

አዎን። ገቢዎ ከጨመረና ጉዳዮን እንደገና ከመረመረ በኋላ፤ የሚከፍሉትን የቤት ኪራይ በዛው መጠን ያስተካክላል። የቤት ኪራያቸው ዋጋ በመንግስት የጎደሉ ቤቶች፤ በዚህ በኮቪድ ግዜ፤ የቤት ኪራይን የማጉደል ህግ አይመለከታቸውም።

**በመንግስት ቤት ውስጥ ነው የምኖረው። የዲሲ የቤቶች ባለስልጣን ( DCHA) ኪራይ መክፈል ቢያቅተኝ ከቤቱ ሊያባረኝ ይችላልን ?**

የቤት ኪራይ ባለመክፈልዎ ባለስልጣኑ (DCHA ) ሊከሶት ይችላል ግን በአሁኑ ግዜ አይደለም።አዲስ የመንግስት ህግ፤ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር በአሁኑ ግዜ ፤ እስከ ነሃሴ 24 ቀን 2020 ድረስ፤ የቤት ኪራይ ስላልተከፈለ፡ ተከራይን ለማባረር፤ አዲስ የክስ ጥያቄ ማስገባት አይችልም ይላል። ምንም ነገር ከማድረጉም በፊት የ 30-ቀናት ማስጠንቀቃ ወረቀት መስጠት አለበት። በተጨማሪም፤ አዲስ የዲሲ ህግ፤ ከቤት የማስወጣት ጉዳዮች ሁሉ እንዲቆሙ አድርጓል።In addition, a new D.C. law stops all new eviction case filings. ይህ ግዜያዊ ህግ ነው። የሚቆይበት ግዜም ይህ የኮሮና በሽታ እስካለበት ግዜና ካለቀም በኋላ ለ60 ቀናት የሚቆይ ነው።This is a temporary law, which will be in effect during the current public health emergency and for 60 days after it ends. Currently the D.C. law expires as of September 22, 2020.

**ከኮቪድ በፊት፡ በኩፖኑ ፕሮግራም፤ ከቤት መውጣት አለባቸው የሚል ሃሳብ ያለበት ወረቀት አግኝቼ ነበር። እኔም ጉዳዬ እንዲሰማ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ነበረኝ፡ አሁን የሚሆነው ምንድነው?**

የኩፖን ማሳረግያ ቀጠሮች ሁሉ ለግዜው ወደ ሌላ ቀን ተላልፈዋል። የዲሲ የቤቶች ባለስልጣን (DCHA) በሪሞት ጉዳዮ እንዲሰማ መፈለጎን ለማወቅ ከ እርስዎ ግንኙነት ይፈጥር ይሆናል። ይህ የግዴታ አይደለም፤ አዎን የሚል መልስ መስጠት ግዴታ አይደለም።If you አልፈልግም ካሉ ባለስልጣኑ( DCHA) በሌላ ግዜ በአካል የሚገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል።ay

**ከኮቪድ-19 (Covid-19 በፊት፤ መልሼ እከፍላልሁ የሚል ስምምነት ከዲሲ የቤቶች ባለስልጣን (DCHA) ጋር ፈርሜአለሁ። አሁን ግን ስራዬን ስላጣሁ መክፈል አልችልም። ምን ላድርግ?**

ከላይ የተጻፉትን የኢሜል አድራሻዎችን በመጠቀም፤ ወድያውኑ ገቢዎን እንዳጡ ሪፖርት ማድረግ አለቦት። የዲሲ የቤቶች ባለስልጣን (DCHA) እነኚህን ጉዳዮች አንድ በአንድ እንደ የሁኔታቸው እንመለከታቸዋለን ብሏል። ስለዚህ ገቢዎን ማጣትዎን ወድያውኑ ሪፖርት ማድረግ ጉዳዮን ይጠቅማል።

አዲስ የዲሲ ህግ እንደሚለውም፡፤ ተከራይ፤ በዚህ በኮቪድ-19 (Covid-19) ምክንያት የቤት ኪራይ የመክፈል ችግር ሲያጋጥመው፤ አከራይ፤ አንድ ዓይነት የአከፋፈል ዕቅድ ለተከራይ ማውጣት አለበት ይላል።

***

ጉዳዮን በተመለከተ ህጋዊ ምክር ቢፈልጉ፤ ከሊጋል ኤድ( Legal Aid )ጋር ተገናኙ። በኖርትዌስትና በኖርትኢስት ( Northwest and Southeast) ያሉት ጽህፈት ቤቶቻችን በአሁኑ ግዜ ለህዝብ ዝግ ናቸው። ይሁንና በስልክና በኦንላይን ግን ክፍት ነን። የተከራዮች አስቸኳይ መስመር (Tenant Hotline) በስልክ ቁጥር 202-851-3388 በመደወል ወይም online በመግባት ምክርና ስለ ኪራይ ቤቶች አጠቃላይ መረጃ ቢፈልጉ፤ ለቤት ኪራይ ጉዳይ ደግም እርዳታ ከፈለጉ ያመልክቱ።